# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ


**ጸሐፊው**: Edward Hughes
**የተተረጎመው**: Abel Eshetu
**ምሣሌ አቅራቢው**: Byron Unger; Lazarus
**ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው)**: E. Frischbutter; Sarah S.



ታሪክ 39 ከ 60 ዎቹ መሃከል

**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


**አማርኛ** Amharic

ኢየሱስ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል።በሽተኞችን ፈውሷል፣ ለተቸገሩት ሰላምን ሰጥቷል፣የእግዚአብሔርንም ቃል አስተምሯል።



1

በርካታ ሰዎች ኢየሱስ እንዲፈውሳቸውና እንዲረዳችው ወደ እርሱ መጡ፤ ስለሆነም በዚህ አገልግሎት የሚረዱትን አስራ ሁለት ሐዋርያትን ለመምረጥ ወሰነ።



2


በጣም ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ሲኖራችሁ ወደ እግዚአብሔር ትጸልያላችሁ? ኢየሱስ ግን ጸልዮ ነበር! ብቻውን በተራራ ላይ ይጸልይ ነበር። እስኪመሸ ድረስ ይጸልይ ነበር።
3


ሌሊቱን ሙሉ የጸለየበት ጊዜ ነበር።
4


ሲነጋም ኢየሱስ ተከታዮቹን ወደ እርሱ ጠራቸው። ከእነርሱም መካከል አብረውት እንዲያገለግሉ አስራ ሁለት ሐዋርያትን መረጠ።
5


መጀመሪያ የመረጣቸው ወንድማማቾቹን ስምዖን ጴጥሮስንና እንድርያስን ነበር።
6


ያዕቆብና ዮሐንስም የአሳ ማጥመጃ መረባቸውን ትተው ነበር የተከተሉት።
7


ፊልጶስ፣በርተለሜዎስ፣ማቴዎስ፣ቶማስ፣ቀናተኛው ስምዖን፣የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ እንዲሁም ኢየሱስን የሸጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ከተመረጡት መካከል ይገኙበታል።
8


የእግዚአብሔርን ቃል
መታተዝ ቤትን በአለት
ላይ እንደመስራት ነው
ብሎ ኢየሱሰ
አስተምሯል።
9


ጽኑ ማዕበል ቢመታው ይህ
አይነቱ ቤት አይፈርስም።
10


ቃሉን አለመታዘዝ ደግሞ ቤትን በአሸዋ ላይ እንደመስራት ሲሆን
ማዕበል በመጣ ጊዜ ይህ ቤት ቶሎ ፈራሽ ይሆናል።
11


አንዳንዶቹ የኢየሱስ ትምህርቶች
ቀላል አልነበሩም። “ቀኝህን
ለሚመታህ ግራህን ስጥ”፤
“ጠላቶቻችሁን ውደዱ”
ብሎ አስተምሯል።
12


ኢየሱስ እንደሚለው
ለመኖር የእግዚአብሔር
እርዳታ ያስፈልጋል።
13


አንዳንድ ፈሪሳውያን ለታይታ
እንደሚያደርጉት በአደባባይ
ሳይሆን በስውር መጸለይ
እንደሚገባ ኢየሱስ አስተምሯል።
14













ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4-7
፤ የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 1
፤የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 6

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16